# የበጎቹ እረኛ

ሰርቶ እንደሚበላ ፣ እንዳመጣ ለፍቶ
በርጥባን ያበጠው ፣ ኮሮጆውን ሞልቶ
የጉድ አገር ገንፎ ፣ ደሃው ደሃን ጠልቶ
ዜጋን ማሰቃየት ፣ ደሃው ላይ ቀረርቶ
እኔ ትብስ አንተ ፣ መተዛዘን ቀርቶ
መጃነን በባዶ ፣ ምስኪኑን ተጋፍቶ ።

ባጀት በልመና ፣ አስቦ የሚያሰላ
የታወቀው ለማኝ ፣ ሙያውን የጠላ
የእርዳታ ስንዴ ፣ ጠፍጥፎ እየበላ
በርጥባን የሚኖር ፣ ደሃን የሚያጉላላ
ቀላውጦ እየኖረ ፣ ምስኪን ላይ ሸለላ
ታይቶም አይታወቅ ፣ ከአብይ መንግሥት ሌላ ።

የደሃውን ጎጆ ፣ በግፍ ያፈረሰ
ህፃን ሽማግሌን ፣ ደም እያስለቀሰ
መንደሬን አቆሸሸክ ፣ አልይህ ተብሎ
ቤቱን አፍርሶበት ፣ ጎዳና ተጥሎ
የት ይሂድ የት ይግባ ፣ ከገዛ ሃገሩ
ለማን አቤት ይባል ፣ ለማን ይናገሩ
ልክ ያጣ ጭካኔ ፣ በበደል ላይ በደል
ያሁኑ ይባስ መጣ ፣ ሰውን በቁም መግደል ።

ልጅ እንዳያሳድግ ፣ ኑሮን አሸንፎ
በሰቆቃ ኑሮ ፣ በጠኔ ተገርፎ
ለዘይት ለዳቦው ፣ ሁሌ ተሰልፎ
ብዙ ዘመናትን ፣ የከፋን ቀን አልፎ
ቀን ያልፋል እያለ ፣ ተስፋን ተደግፎ
እሱ አልበቃ ብሎ ፣ ዜግነት ተገፎ
ይሳደዳል ዛሬም ፣ ከኖረበት አርፎ ።

ቅጥ ያጣ አስተዳደር ፣ በዘመነ ኬኛ
በነ አብይ ግዛት ፣ ፍርደ ገምድል ዳኛ
ጠባቂ ታዘለት ፣ ዘራፊ ቀማኛ
ታጅቦ ይሄዳል ፣ ልክ እንደ ሰርገኛ
ሰላም ሰባኪው ግን ፣ ተብሎ ሴረኛ
በግፍ ተጎትቶ ፣ ይሆናል እስረኛ
ተኩላው ሆኗል ዛሬ ፣ የበጎቹ እረኛ ።

ታዛቢው

August 19, 2019